| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ያንድ ፡ ሰው ፡ ሽግግር ፡— የሽግግር ፡ ክስረት ፤ የክስረት ፡ ሽግግር" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መጋቢ.ት ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-004 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## ያንድ ፡ ሰው ፡ ሽግግር ፡— የሽግግር ፡ ክስረት ፤ የክስረት ፡ ሽግግር ።



ዛሬ ፥ መላ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ በኹለት ፡ የውንብድና ፡ ኀይሎች ፡ ጣምራ ፡ ጭቈና ፡ ሥር ፡ ትገኛለች ፡—

- በሰሜናዊ ፡ ክፍሏ ፥ በባሕር ፡ ምድርና ፡ በደንከል ፡ ግዛቶቿ ፥ የ"ሻዕቢ.ያ" ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፥ አለሕገ ፡ መንግሥትም ፡ ኾነ ፡ አለምርጫ ፥ የኢ.ትዮጵያን ፡ ከፊል ፡ ሕዝብ ፡ ደፍጥጦ ፣ ከፊል ፡ ምድሯንም ፡ ዐንቆ ፡ ይዟል ፤
- በቀረው ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ክፍል ፥ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፥ በባዕድ ፡ ሠራሹና ፡ በሕገ ፡ ወጡ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፥ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ አላግባብ ፡ ተሰቅሎ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ፀረ ፡ ሀገር ፡ ዘመቻን ፡ ሲ.መራ ፥ በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ በሀገሪቱ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ ላይ ፡ ለዘለቄታው ፡ ሲ.ውስንና ፡ ከባዕዳን ፡ ሲ.ደራደር ፡ ይታያል ።

ኹለቱም ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በሕዝብ ፡ ሰቈቃውና ፡ ጩኸት ፡ ተሞልተዋል ፤ ኹለት ፡ ዐምባ ፡ ገነኖች ፥ በፈረቃ ፥ አንዱ ፡ ነጂ ፣ ሌላው ፡ ተነጂ ፡ እየኾኑ ፥ በአስመራ ፡ እና ፡ በዐዲ.ስ ፡ አበባ ፡ ጐዳናዎች ፡ መሽከርከርን ፡ አስለምደዋል ።

አሮጌው ፡ የአስመራው ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ኢ.ሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡— "አክ!" ፡ ብሎ ፡ አንቅሮ ፡ የተፋውን ፡ "ምርጫ" ፥ የዐዲ.ስ ፡ አበባው ፡ ለማጅ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ ዐቢ.ይ ፡ አሕመድ ፡ ደግሞ ፥ የ"ምርጫ"ን ፡ ተስፋ ፡ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እያለማ ፥ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ የሀገር ፡ ፈረሳ ፡ ሴራውን ፡ ሲ.ዶልት ፡ ዐድሮ ፡ ሲ.ያስፈጽም ፡ ይውላል ፥ ሲ.ሞዳሞድም ፡ ያመሻል ።

"አሯሯጮች" ፡ ብሎ ፡ የተሣለቀባቸው ፣ ነፍሳቸውን ፡ የሼጡ ፡ "ፖለቲከኞች"ም ፥ ያች ፡ የፈረደባት ፡ ለምርጫ ፡ ተሳታፊዎች ፡ ፓርቲዎች ፡ እንድትከፋፈል ፡ ከምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ የምትላክ ፡ የ 96 ፡ ሚ.ልዮን ፡ ብር ፡ ድጐማ ፡ እንዳትቀርባቸው ፥ ዐዲ.ስ ፡ አበባ ፡ ቍጭ ፡ ብለው ፡ ቊማሩን ፡ ተያይዘውታል ። የነርሱ ፡ ሲ.ገርመን ፥ አላግባብ ፡ ታስረዋል ፡ ብለን ፡ የምናከብራቸው ፡ የ"ፓርቲ" ፡ መሪዎች ፡— "ከእስር ፡ ተፈተን ፡ ከምርጫው ፡ ብንሳተፍ ፥ አኹንም ፡ ቢ.ኾን ፡ እናሸንፋለን" ፡ ሲ.ሉ ፡ በየዋህነት ፡ ለ"ምርጫ ፡ ቦርዱ" ፡ ዱልዱም ፡ አመራር ፡ የላኩት ፡ ምልጃ ፡ እጅጉን ፡ አስደምሞናል ። ለ"ፖለቲከኞች" ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ መልእክት ፡ አለን ፡— በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ መሠረት ፡ ከሚ.ጠራ ፡ ምርጫ ፡ በመሳተፍና ፡ በ"ማሸነፍ" ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢ.ነት ፡ መቼም ፡ ቢ.ኾን ፡ አይገኝም ፤ ውጤቱ ፡ ያው ፡ የሕዝብን ፡ እግዚ.እና ፡ የረመረመ ፡ ዳግም ፡ ዐምባ ፡ ገነንነት ፡ ይኾናል ። ወቅቱ ፥ የሕዝብ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚ.እና ፡ የሚ.ረጋገጥበት ፡ የትግል ፡ ወቅት ፡ እንጂ ፥ የተገላቢ.ጦሽ ፥ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች" ፡ ለጌትነት ፡ የሚ.ሰትፉበት ፥ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ ላሽከርነት ፡ የሚ.ያደገድግበት ፡ አይደለም ። ትኽክለኛ ፡ ምርጫ ፡ የሚ.ኖረው ፥ ሕዝብ ፡ ገዢ.ነቱን ፡ ባስከበረበት ፡ ኹኔታ ፥ ራሱ ፡ ባጸደቀው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፥ "የፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች"ን ፡ ለአሽከርነት ፡ ቅጥር ፡ ለማወዳደር ፡ ሲ.ፈቅድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**የኢ.ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ** ፥ ጧት ፡ ማታ ፡— "ሕዝቦች" ፡ እያለ ፡ የሚ.ከድኽ ፥ በዚ.ህ ፡ ባጥፊ ፡ ሕገ ፡ ውንብድና ፡ መሠረትም ፡— "ከምርጫ ፡ ተሳትፎ ፡ እታደግኻለኹ" ፡ ሲ.ል ፡ የሚ.ዋሽልኽ ፡ አላዋቂ ፡ "ፖለቲከኛ" ፥ በስሕተቱ ፡ ቢ.ጸና ፥ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የመሥራት ፡ የእግዚ.እና ፡ መብትኽን ፡ እንደ ፡ ካደ ፡ ዐውቀኽ ፥ ተራኽን ፡ ይህን ፡ "የምኝ ፡ ፖለቲካ" ፡ በመካድ ፥ እግዚ.እናኽን ፡ ለማስከበር ፣ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ ለመሥራትና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥትኽን ፡ ለመመሥረት ፥ ከጥንት ፡ በወረስከው ፡ ልማድኽ ፥ በመላ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፥ ከቀበሌ ፡ እስከ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በእየዕርከኑ ፡ መሪዎችኽን ፡ እየሠየምኽ ፡ ለትግል ፡ ቈርጠኽ ፡ በአንድነት ፡ ተነሥ ፣ ተደራጅ ፣ ታገል ❖

እግዚ.እናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢ.ትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢ.ትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።